# የአባላዘር ተላላፊ በሽታዎች እውነት ነገሮች

Gonorrhea (“Clap”) - Amh

## ጨብጥ (ጎኖርያ)
## (በኒሰርያ ጎኖሪያ ባክተርያ ምክንያት የሚነሳ)

### የበሽታው ምልክት

የጨብጥ ምልክት፣

- በበሽታው ከተለከፉ ከ2-7 ቀን በኋላ
- በሴቶች ቀላል ሊሆስ ወይም ላይታይ ይችላል

የሴቶች ጨብጥ ምልክቶች፣

- ከልክ በላይ የብልት መድማት፤ ማሳከክ
- ሽንት ሲሸኑ ማቃጠልና ማመም
- በወር አበባ ግዜ ያልታሰበ ደም መፍሰስ
- በታችኛው ሆድ ውጋትና ማመም
- የቂጥ ማመም፣ ማሳከክና ፈሳሽ መውጣት

የጨብጥ ምልክቶች በወንዶች ላይ፣

- ከወንድ ብልት የሚወጣ ነጭ ወፍራም ፈሳሽ (መግል)
- ሲሸኑ ማቃጠል፣ ማመም ወይም ማስቀመጥ
- የቂጥ ማመም፣ ማሳከክና ፈሳሽ መውጣት

### መተላለፍ

ጨብጥ የሚተላለፈው፣

- በሴት ብልት ግብረስጋ
- በአፍ ግብረስጋ
- በፊንጢጣ ግብረስጋ
- ከታመመች እናት ወደ አዲስ የተወለደ ህጻን

### ጣጣውና የሚያስከትለው ችግር

ጨብጥ ሳይታከም ከቀረ፣

- የማህጸን ማቃጠል በሽታ
- ከማህጸን ውጭ ማርገዝ (በቱቦው)
- በወንድና ሴት ያለመውለድ
- የአካል መገጣጠምያ ማመም
- ወደ ግብረስጋ ተካፋዮች ማጋባት

ጨብጥና እርግዝና፣

- አዲስ ወደ ተወለደው ህጻን ሊጋባ ይችላል
- አዲስ ወደ ተወለደው ህጻን የዓይን በሽታ ይፈጥራል
- ወደ ሌላ አካል ይተላለፋል

### መከላከል

የጨብጥን መጋባት የሚቀንሱ አስተያየቶች፣

- ላቴክስ ኮንዶም በደንብና፣ ሁሉግዜ፣ ከተጠቀሙባቸው የጨብጥ መተላለፍን ሊቀንሱ ይችላሉ
- የሴት ብልትና አፍ ግብረስጋ ሲያደርጉ ሁሉግዜ ላቴክስ ኮንዶም ይጠቀሙ
- የወንድ ብልትና አፍ ግብረስጋ ስያደርጉ ኮንዶም ይጠቀሙ
- የሴት ብልትና አፍ ግብረስጋ ካደረጉ ኮንዶሙን በሁለት በመክፈል ይጠቀሙ
- የግብረስጋ ተካፋዮችዎ ይቀንሱ
- ከታመሙ ተካፋዮችዎን ያስታውቁ
- ተካፋዮች አንድላይ እንዲመረመሩና እንዲታከሙ ያድርጉ

### ሕክምና

የጨብጥ ሕክምና፣

- ከሃኪም ተገቢውን መድሃኒት በማግኘት ሊድን ይችላል
- ተካፋዮች አንድላይ መታከም አለባቸው

ማስታወሻ፣ እንደገና ሊታመሙ ይችላሉ

ለተጨማሪ ማብራርያ በሚከተለው ይጠይቁ፣


Infectious Disease Epidemiology, Prevention and Control Division
STD and HIV Section
Minnesota Department of Health
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-5414; (651) 201-5797 TTY


Minnesota Family Planning and STD Hotline
1-800-783-2287 ድምጽ /TTY

CDC National STD and AIDS Hotlines
1-800-227-8922; 1-800-243-7889 TTY

በ Minnesota Department of Health, STD and HIV Section የተዘጋጀ - ጥር 2002 rev 2006